# <u>አዋጅ ቁጥር …../2008</u>

## <u>የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ</u>

በሀገሪቱ በመተግበር ላይ ያሉ  የዱር ሕይወት ህጎች አሁን ካለው ዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታ ጋር   ባለመጣጣማቸው ባለባቸው ክፍተት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣውን የዱር ህይወት ሀብት የመጥፋት አደጋ ለመግታት ባለመቻሉ፤

ሀገሪቱ ከዱር ሕይወት ሃብት የምታገኘውን ስነምህዳራዊ፤ ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ በማጎልበት ንዑስ ዘርፉ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂና ለድህነት  ቅነሳ የበኩሉን አስተዋፅዖ   እንዲያበረክት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ  የሚኖረውን ህብረተሰብ፣ የግል ባለሃብቶችና አጋሮችን በዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ቀጥተኛ ተጠቃሚና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዱርሕይወት ሀብት አጠባበቅ፣ አንክብካቤና አጠቃቀምን በሚመለከት ሀገሪቱበዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የገባቻቸውን ግዴታዎች በተሻለ መልኩ መፈጸም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለዱር ሕይወት እየተደረገ ያለውን ጥበቃና ቁጥጥር በሚፈለገው መልኩ ውጤታማ ለማድረግ  ጠንካራ፣ አሳታፊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ አስፈፃሚ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

DRAFT

# ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር .....2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የዱር እንስሳት" ማለት ከቤት እንስሳት በስተቀር በሕይወት ያሉ ወይም የሞቱ የጀርባ አጥንት ያላቸው ወይም የሌላቸው እንስሳትማለት ነው፤
2. "የዱር ሕይወት" ማለት ዱር ድንበራቸው ተለይቶ በተከለሉ የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ የዱር እፅዋትና እንስሣት ማለት ሲሆን ከአገር ወደ አገር የሚሰደዱትንና በጊዜያዊ መልክ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ዝርያዎች ይጨምራል፤
3. "የዱር እንስሳት ውጤት" ማለት የማንኛውም የዱር እንስሳ ናሙና ወይም የእንስሳውአካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ፀጉር፣ ላባ ወይም ኀፍላው ሲሆን፤ ከእነዚህ የተሠሩ ውጤቶችንና ከእንስሳው መኖሪያ አካባቢ የተገኙትን የወፍ ጎጆ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ልጣጭ፣ አበባ፣ ማርና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤
4. "የዱር ሕይወት የመኖሪያ አካባቢ" ማለት የየብስ፣ የውሃ አካል ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር ሕይወት የሚኖሩበት የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጪ ያለ ሥፍራ ነው፤
5. "የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታ" ማለት ለዱር ሕይወት ጥበቃ በሕግ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የዱር ሕይወት መጠለያዎችን፣ የዱር

DRAFT

ሕይወትጥበቅክልሎችን፤ የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን፣ የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን፣ ህይወታዊ ጥብቅ ክልሎች ማለት ነው፡፡

6. "የብሔራዊ ፓርክ" ማለት የዱር ሕይወትንና ተያያዥ የየብስና የውሃ የተፈጥሮ ሃብቶችንለመጠበቅና የአካባቢውን ሥነ-ውበታዊና ሥነ-ምህዳራዊ እሴት በመንከባከብ የቱሪዝምና ሣይንሳዊ እውቀትፋይዳ እንዲያበርክት የሚከለል ቦታ ነው፡፡

7. "የዱር ሕይወት መጠለያ" ማለት በዋናነት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ለተሰጣቸው የዱር ሕይወትዝርያዎች ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ሆኖ ሌሎችምበውስጡ የሚገኙትን የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ዝርያዎች ጭምር ለመጠበቅ የሚከለል ቦታ ነው፤

8. "የዱር ሕይወት ጥብቅ ክልል" ማለት ለዱር ሕይወት ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ሆኖ በሥፍራው የነበሩ ሰዎች የዱር ሕይወትን እየተንከባከቡ በቦታው እንዲኖሩ የሚፈቀድበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም መጠለያ ደረጃ ሊያድግየሚችል የጥበቃ ቦታ ነው፤

9. "የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታ" ማለት በመንግሥት ወይም በኮንሴሽን ያልተያዘ በአካባቢው ሕብረተሰብ የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥራ የሚሠራበት ሥፍራ ነው፤

10. "የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌ" ማለት ለዱር ሕይወት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፤

11. "ህይወታዊ ጥብቅ ክልል"ማለት ሕይወታዊና ባህላዊ ስብጥርን መሰረት ያደረገ የአካባቢውን ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በማጣጣም ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ የሚከናወንበት ሥፍራ ነው፤

12. "የዱር እንስሳትእርባታ"ማለት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር በግዥ የተገኙ ወይም ከዱር የተሰበሰቡ የዱር እንስሳትን በተፈጥሮ አካባቢያቸው ወይም ከተፈጥሮ አካባቢያቸው ውጪ ተንከባክቦ በማሳደግና በማራባት በፍጆታዊና

DRAFT

ኢ-ፍጅታዊ አጠቃቀም አማካኝነት ጥቅምላይ ለማዋል፣ ሀብቱን ለመጠበቅ እና ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥየሚከናወን ተግባር ነው፤

13. "ኢ-ዘቦታ ጥበቃ" ማለት የዱር ህይወትን ከተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸዉ ውጭ የመጠበቅ እና የመንከባከብስርዓት ነዉ፡፡

14. "ዘቦታ ጥበቃ" ማለት የዱር ህይወትን በተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸዉ ውስጥ የመጠበቅ እና የመንከባከብ ስርዓት ነዉ፡፡

15. "መዋዕለ እንስሳት"ማለት በታጠረ አካባቢ በኢ-ዘቦታነት ተከልሎ የዱር እንስሳት የሚጠበቁበትና ለህዝብ ዕይታ የሚቀርቡበት ሥፍራ ነው፡፡

16. "የዱር ሕይወት ንግድ" ማለት የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤቶችን ወደውጭ መላክ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት መልሶ ወደውጭ መላክ ወይም የዱር ህይወትን የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት ህጋዊ የንግድ ልውውጥ ነው፡፡

17. "የዱር ሕይወት ቁጥጥር ሠራተኛ" ማለት የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶችን በሚመለከት የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን እንዲቆጣጠር በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡

18. "ማደን" ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለማቁሰል፣ ለማጥፋት፣ ለማስፈራራት፣ ለማባረር፣ ለመያዝ ወይም የዱር እንስሳትን ላባ፣ እንቁላል ወይም ሌሎች ውጤቶችንለመውሰድ የሚወሰድ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ነው፡፡

19. "ማጥመድ" ማለት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የዱር እንስሳትን ከነ ህይወታቸው መያዝ ነው፡፡

20. "ዝርያ" ማለት በተፈጥሯዊ ሥነ-አካልና ዘረ-መል አመዳደብ መሠረት በአንድ ሥነ-ሕይወት ምድብ ውስጥ አባል ሆኖ የተመደበ የዱር ሕይወት ዓይነት ሲሆን፣ ንዑስ ዝርያዎችንም ይጨምራል፡፡

DRAFT

21. "ዓለም አቀፍ ስምምነቶች" ማለት ሕልውናቸው ለዕልቂት አደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳትና እፅዋት ዓለም አቀፍ ንግድ ስምምነት (ሳይተስ)፣ የተሰዳጅ የዱር እንስሳትጥበቃ ስምምነት (ሲ.ኤም.ኤስ)፣ የአፍሪካ ኤሮኤዥያ የውሃ አዘል አዕዋፋት ስምምነት (ኤይዋ)፣ ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሕብረት (አይ.ዩ.ሲ.ኤን) እና ሌሎች ሀገሪቱ የዱር ሕይወትን አስመልክቶ በቀጣይ የምትፈርማቸው ስምምነቶች ማለት ነው፡፡

22. "ብርቅዬ የዱር ሕይወት ዝርያ" ማለት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ሀገሪቱ በብቸኝነት የምትታወቅባቸው የዱር ሕይወት ዝርያዎችና ንዑስ ዝርያዎች ማለት ነው፡፡

23."ሕልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች" ማለት በአይ.ዩ.ሲ.ኤን መስፈርት መሠረት በተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው ለአደጋ የተጋለጡና ከምድረ-ገጽ ለመጥፋት የተቃረቡ የዱር ሕይወት ዝርያዎች ማለት ነው፤

24."ፍጆታዊ አጠቃቀም" ማለት የዱር ህይወት ከመኖሪያ ቦታው በመውሰድ ወይም በስፖርታዊ አደን፣ በራንች ወይም ዕርባታ በማሳደግ ለውጤታቸው (ሥጋ፣ ቆዳ፣ ላባ፣ቀንድ፣ጥርስ) ሲባል በመግደል የመጠቀም ስልት ነው፡፡

25."ኢ-ፍጆታዊ አጠቃቀም" ማለት የዱር ህይወት ከመኖሪያ ቦታቸው ሳይወሰዱና ሳይገደሉ የመጠቀም ስልት ሲሆን የዱር እንስሳት ማስጎብኘትን፣ ፊልምና ፎቶ ግራፍ ማንሳትን ያካትታል፡፡

26. "ፈቃድ" ማለት በዱር ሕይወትና ውጤቶቻቸው ላይ ለሚደረግ ማንኛውም ሕጋዊ ንግድ ወይም ለባለቤትነት የሚሰጥ ፈቃድ ሆኖ የዱር እንስሳትን የማደን፣ የማሳደን፣ የማርባት፣ የመያዝ፣ የጐፍላ ሥራ የመሥራት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ የዱር ሕይወትን በሕይወት የመነገድ፣ የዱር ሕይወትን ፊልም የመቅረጽ ፈቃድን፣ ጥናትና ምርምርን ለማካሄድእንዲሁም የሌሎች የአጠቃቀም ዓይነቶችን ፍቃድ ያካትታል፤

27. "ነጋዴ" ማለት በህግ ከተከለከሉት ውጭ ያሉትን የዱር ሕይወት ውጤትና ከዱር ሕይወት ውጤት በተሠሩ ዕቃዎች የንግድ ተግባር እንዲያከናውን የተፈቀደለት ሰው ሲሆን በዱር ሕይወትውጤቶችየሚዘጋጁ ልዩ ልዩ ቅርጾችን

DRAFT

ለትርዒት የሚያሰናዳ ወይም ከአደን ውጤቶች ዕቃን የሚያዘጋጅ ወይም በሌላ መንገድ የሚሠራን ሰው ይጨምራል፤

28. "ገቢ" ማለት ከዱር ሕይወትና መኖሪያ አካባቢያቸው፣ ፊልም ቀረጻ፣ ንግድ፣ ጥናትና ምርምር፣ ጉብኝትና ካምፕ፣ የዱር እንስሳት አደን እና ከልዩ ልዩ ፈቃዶችና የፈቃድ ዕድሳቶች፤ ከተለያዩ ቅጣቶች እንዲሁም ከአዳዲስ የዱር ሕይወት አጠቃቀም ዓይነቶች የሚሰበሰብ ገቢ ነው፡፡

29. "መሣሪያ" ማለት የዱር ዕፅዋትን ለመቁረጥ፣ የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ለመያዝ ወይም እንዳያመልጡ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ጥይት የሚተኩስ መሣሪያ፣ጳርት ጋን፣ ተወርዋሪ ሚሳይል፣ ፈንጂ፣ ቀስት፣ጹላ፣ ስለት፣ ወጥመድ፣ መረብ፣ ጉድጓድ፣ መርዝ፣ ኬሚካል፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ለዚህ ተግባር የሚውል መገልገያ ነው፣

30. "የአየር መንኮራኩር" ማለት በሰው ወይም ያለ ሰው የሚንቀሳቀስ ሆኖ በሞተር ኃይል በአየር ላይ በሚነዳ አካል ብቻ ሳይወሰን ማናቸውም በአየር ላይ ተንሳፋፊ አካል ወይም አይሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ድሮን እና ሌሎችም ማለት ነው፤

31. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ መሠረት ሕጋዊ ሠውነት የተሰጠው አካል ነው፤

32. "ሚኒስቴር" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤

33. "ባለሥልጣን" ማለት የዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

34. "ክልል"ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

35. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

DRAFT

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የኢትዮጵያን የዱር ሕይወት ሀብት ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፤
2. ሀገሪቱ ከዱር ሕይወት ሀብት የምታገኘውን ስነምህዳራዊ፤ ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ ማሳደግና ቱሪዝምና ኢንቨስትመንትንማስፋት፤
3. በጥብቅ ቦታዎች ዙሪያ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችከተፈጥሮ ሀብቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚእንዲሆኑ በማድረግ በዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማስቻል፡፡
4. ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍና ቅንጅታዊ አሠራርን በመፍጠርበዱርሕይወት ሀብት ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ መቀነስ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን</u>

4. <u>ስለመቋቋም</u>
   1. የኢትዮጵያ የዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንየሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

5.<u>*ዋና መሥሪያ ቤት*</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የጥበቃ ቦታ ጽሕፈት ቤቶች በሌሎች ሥፍራዎች ላይ ያቋቁማል፡፡

DRAFT

6. *ዓላማ*

የኢትዮጵያ የዱር ሕይወት ሀብትን በህብረተሰብና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በመጠበቅ፣ በማልማትና በማስተዋወቅ ለሀገራችንና ለዓለም ህብረተሰብ ዘላቂ ስነ-ምህዳራዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ እና ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ ነው፡፡

7. *የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት*

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የዱር ሕይወት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ የፖሊሲና የሕግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
2. የዱር ሕይወት ሀብቱን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲሁም የአጋሮችን ድጋፍ ለማጠናከር ያስችለው ዘንድ በህግ በሚወሠነው መሠረት ትረስት ፈንድ ያቋቁማል፤
3. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎችን በመከተል በመንግሥት በሚፀድቀው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤
4. ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በዱር ህይወት ሀብቱ ላይ የሚፈፀመውን ከፍተኛወንጀል ለመከላከል የሚያስችል የጥበቃና ቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ደረጃቸውን የጠበቁ ወታደራዊ መሣሪያዎችና ዩኒፎርሞች እንዲሟሉ ያደርጋል፤
5. በፌደራል መንግስት ስር የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላል፤በክልል ለሚተዳደሩትም አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
6. በሰው ሰራሽ ጫና ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታ አካባቢዎች ለህብረተሰቡ አማራጭ የኑሮ ዘዴዎችን በመፍጠርና የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢውን መልሶ እንዲበለፅግ በማድረግ እንዲያገግሙ ያደርጋል፤

7. በዱር ሕይወት ሀብት ላይ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

8. በየትኛውም የዱር ህይወት መኖሪያ አካባቢና በሀብቱ ላይ የመጥፋት ስጋት መድረሱ በጥናት ሲረጋገጥ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

9. በዱር ህይወትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ውስጥ በባለሥልጣኑ ፈቃድ በውጭ አገር ዜጎች ለሚከናወን ተግባር ፈቃድ ይሰጣል፤ ተገቢውን ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፤

10. በፌዴራል መንግሥት በሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚቋቋሙየቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ሌሎች የአጠቃቀም ፈቃዶችን ይሰጣል፤ ተገቢውን ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፤

11. ማናቸውንም የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

12. የዱር ሕይወትናውጤቶቻቸውን በተመለከተየተሰጠ ፈቃድ ለታለመለት ዓላማና ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ውጤቱንም ይከታተላል፤

13. ከክልሎች ጋር በመመካከር ከዱር ሕይወት ሀብት የሚገኘው ገቢ ለተፈጥሮ ሀብቱ ጥበቃና ለአካባቢው ህብረተሰብ ቀጥተኛ ጥቅም እንዲውል ያደርጋል፤ ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል፤

14. የዱር ሕይወትና ውጤቶቻቸውን ህገወጥ ዝውውር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር አስፈላጊውን ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ይቆጣጠራል፤

15. ባለሀብቶች በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፤ ጥራታቸውን የጠበቁ የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲያመርቱ የዱር ህይወት አጠቃቀም ስብጥሮችን በማስተዋወቅ እንዲተገበር ያደርጋል፤

DRAFT

16. ከጎረቤት አገሮች ጋር አዋሳኝ በሆኑና የዱር እንስሳት በሚዘዋወሩባቸው ሥፍራዎች የተቋቋሙ ድንበር ዘለል የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ሥርዓተ አያያዝን ያጠናክራል፤ አዳዲስ ቦታዎችም እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤

17. በሀገሪቱ ብቻ የሚገኙ እንዲሁም ቁጥራቸው መናምኖ ለመጥፋት አደጋ የተጋለጡ የዱር ህይወት ዝርያዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይንከባከባል፤ አስፈላጊው የጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል፤

18. የዱር ህይወት ልማት፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን መሠረት ያደረገ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የሥልጠናና ምርምር ማዕከል ያቋቁማል፤

19. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች የዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እናየተፈጥሮ ቅርሶች ማስመዝገቢያ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ አካላት ሪፖርት በማቅረብ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤ መስፈርቶቹን ጠብቀው መተዳደራቸውን ያረጋግጣል፤ ለክልሎችም ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

20. ለዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ ዕርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ አካላት ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሠርታል፤

21. የዱር ሕይወት ሀብትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማትም በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል፤

22. የዱር ሕይወትን በተመለከተ በማናቸውም ዓለም አቀፍ ስብሰባ ወይም ጉባዔ መንግሥትን ይወክላል፤

23. የዱር ሕይወት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና ምርምር፣ ሥልጠናና ትምህርታዊ ፕሮግራም ያካሂዳል፤

24. በሰውና በዱር እንስሳት መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ችግሩ የሚቃለልበትንና የሚወገድበትን እርምጃ ይወስዳል፤

DRAFT

25. በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር ሕይወት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ይቆጣጠራል፤

26. በፌዴራል መንግሥት በሚተዳደሩ የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ አሳታፊ የሆነ የልማትና ጥበቃ አሰራር ይዘረጋል፤ ለክልሎችም ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

27. ከባለሥልጣኑ ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሠረት በተቋማትና በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

28. በመንግሥት በፀደቀ ተመን መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፤

29. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፣

30. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

8.<u>*የባለሥልጣኑ አቋም*</u>

ባለሥልጣኑ፣

1.የመማክርት ጉባዔ

2. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾሙም ዋና ዳይሬክተር፣ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል፤

9. <u>ስለመማክርት ጉባዔ</u>

1. የመማክርት ጉባዔው በመንግሥት የሚሠየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸው እንዳግባብነቱ ይወሰናል፤
2. የመማክርት ጉባዔው ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

10. <u>*የመማክርት ጉባዔው ሥልጣንና ተግባራት*</u>

*የመማክርት ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤*

1. ባለሥልጣኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል
2. በዱር ህይወት ልማትና ጥበቃ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ እንዲጨምር የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
3. የዱር ህይወት ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን በየጊዜው ይገመግማል፤

11. <u>*የመማክርት ጉባዔው ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት*</u>

1/ ጉባዔው በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ የጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3/ የጉባዔው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5/ የመማክርት ጉባዔው በሚኒስትሩ የሚሠየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡ ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሠናል፡፡

*10. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>*

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከተውን የባለሥልጣኑን በተግባርና ኃላፊነት ሥራ ላይ ያውላል፤

3. የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

DRAFT

4. ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

5. ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

6. ስለባለሥልጣኑ የሥራ እንቅስቃሴ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

7. ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላለፍ ይችላል፤

10.<u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩተግባርና ኃላፊነት፣</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-

1. የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጠውን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

11.<u>*በጀት*</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፤

12.<u>*የሂሣብ መዛግብት*</u>

1.ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፤

2.የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይመረመራሉ፤

<u>ክፍልሦስት</u>

<u>ስለዱር ሕይወት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም</u>

13.*በፌዴራል መንግሥት የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች፤*

DRAFT

የሚከተሉት የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች በፌደራል መንግሥት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ ይሆናሉ፤

1. ከፍተኛ የዱር ብዝሀ ሕይወት ስብጥር ኖሯቸው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸው ወካይ ሥርዓተ-ምህዳሮችን የያዙ ብሔራዊ ፓርኮችና የዱር ሕይወት መጠለያዎች፤

2. ሀገሪቱ በብቸኝነት የምትታወቅባቸውና ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች መኖሪያ የሆኑ ብሔራዊ ፓርኮችና የዱር ሕይወት መጠለያዎች፤

3. በመልክዓ-ምድር አቀማመጣቸው በሁለትና ከዚያም በላይ ባሉ ክልሎች ውስጥ የሚገኙእንዲሁም ከጎረቤት አገሮች ጋር የሚዋሰኑ ማናቸውም የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች፤ እና

4. ከጎረቤት አገሮች ጋር በስምምነት የሚቋቋሙ ማናቸውም የድንበር ዘለል የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች፡፡

5. ሀገሪቱ በፈረመችው የተሰዳጅ የዱር እንስሳት ጥበቃ ስምምነት ላይ የተካተቱት ተሰዳጅ የዱር እንስሳት በብቸኝነት የሚቆዩባቸው የጥበቃ ቦታዎች፤

14.*__በክልሎች የሚተዳደሩ የዱር ሕይወትየጥበቃ ቦታዎች__*

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13መሠረትበፌዴራል መንግሥት እንዲሠየሙና እንዲተዳደሩ ከሚደረጉት በስተቀር፣ የተቀሩት የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችየሚተዳደሩትበክልሎች ይሆናል፡፡

15. __በተቋማት ወይም በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች__

1. ተቋማት ወይም የግል ባለሀብቶች ከፌዴራል መንግሥትና ከሚመለከታቸው ክልሎች ጋር በሚያደርጓቸው የኮንሴሽን ውሎች መሠረት በአንቀፅ 13

DRAFT

ከተመለከቱት የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉትን እንዲያስተዳድሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

2. የዱር ሕይወት ሀብት ዘላቂ ልማትና ጥበቃንለማስፈን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከቱትን የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደርንለትርፍ ዓላማ ላልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በከፊል ሊሰጥ ይችላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) መስፈርት መሰረት የተሰየሙና የሚተዳደሩ ብሔራዊ ፓርኮችና የዱር ሕይወት መጠለያዎች ለግል ባለ ሃብት ወይም ለግል ድርጅት አይሰጡም፡፡

16.*__በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች__*

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13፣ 14 እና 15 ከተመለከቱት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙ የዱርሕይወት መኖሪያ አካባቢዎች በአካባቢው ሕብረተሰብ እንዲተዳደሩ የሚመለከታቸው ክልሎች ሊፈቀዱ ይችላሉ፡፡

17.*__የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችንስለመሰየም__*

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 የተመለከቱት የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች በሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ዳር ድንበራቸው ተለይቶ ይሰየማሉ፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 የተመለከቱት የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች የሚሰየሙት ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች ይሆናል፡፡
3. የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች የብዝሃ ህይወት ስብጥርና ክምችትን፣ የቱሪስት ፍሰትን እና የመሰረተ ልማት አቅርቦትን መሰረት በማድረግ የተለያየ ደረጃ ይወጣላቸዋል፤

DRAFT

18. <u>ስለዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ሥርዓተ አያያዝ እቅድ እና ከአደጋ ስለመከላከል</u>

1. በሀገሪቱ ለሚገኙ የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች የአስተዳደር፣ የቱሪዝም ልማት፣ የህብረተሰብ አቀፍ ጥበቃና ልማት፣ የጥበቃና ቁጥጥር እና የሥነ ምህዳራዊ ክትትልን እንደአስፈላጊነታቸው እያካተተ የሥርዓተ አያያዝ እቅድ ይዘጋጅላቸዋል፡፡
2. የዱር ሕይወትን ከልዩ ልዩ አደጋዎች ለመከላከል የሚያስችል የጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

19 <u>ስለዱር ሕይወት እና ውጤቶቻቸው ዝውውር</u>

1. በሀገሪቱ ህጎችና በተፈረሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ካልተፈቀደ በስተቀር በማናቸውም ሁኔታ የዱር ሕይወት ወይም ውጤቶቻቸውን በሀገሪቱ የወሰን ግዛት ውስጥ መያዝ፣ ማከማቸትና ከቦታ ቦታ ማዘዋወር የተከለከለ ነው፡፡

2. ባለሥልጣኑ የዱር ሕይወትና ውጤቶቻቸውን ህገወጥ ዝውውር በሀገሪቱ የአየርና የየብስና የውሃ የመግቢያና መውጫ በሮች ላይ ትኩረት በማድርግ ቁጥጥር ያደርጋል፤

3. በማንኛውም በዱር ሕይወትና ውጤቶቻቸው ዝውውር ቁጥር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰውን ተግባር ከባለስልጣኑ ጋር በመተባበር ማስፈፀም ይኖርባቸዋል፤

20. <u>ከህገወጥ ዝውውር ስለተያዙ የዱር ህይወትና ውጤቶቻቸው</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (1) በመተላለፍ ከህገ ወጥ ዝውውር በህይወት የተያዙና ማገገም የሚያስፈልጋቸው የዱር እንስሳት ተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው እስኪመለሱ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ ወይም በባለሥልጣኑ በሚቋቋሙየማቆያ ስፍራዎች እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡

2. በህገ ወጥ መንገድ ተይዘው ማገገም የማያስፈልጋቸው የዱር እንስሳት እንደተያዙ ወደ ተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ይደረጋል፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አገግመው ወደ ተፈጥሮ አካባቢያቸው መመለስ የማይችሉ የዱር እንስሳት በኢዘቦታ እንዲጠበቁና እንዲለሙ ይደረጋል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ከህገወጥ ዝውውር ተይዘው የተወረሱ የዱር ህይወት ውጤቶች አያያዝን በሚመለከት ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 29 በተቀመጠው መሠረት ይፈፅማል፤

*21 ስለዱር ሕይወት አደን*

1. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል የዱር ሕይወት ጥበቃ ተግባሩን ለማከናወንከሚፈጸም አደን በስተቀር ማንኛውም ሰው የአደን ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳትን ማደን የተከለከለ ነው፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመተባበር የዱር እንስሳቱ ስርጭትና ብዛት እንዲሁም ዘለቄታዊነቱን ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ አረጋግጦ የታዳኝ የዱር እንስሳት ኮታን ይሰጣል፤

3. በቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ያለው የዱር ህይወት ሀብትላይ ጉዳት መድረሱንናስነ ምህዳራዊ መስተጋብሩ መናጋቱን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲረጋገጥ በሚኒስቴሩ አቅራቢነት መንግሥት አደኑን በማናቸውም ጊዜ ሊያስቆም ይችላል፡፡

4. የአደን ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሠረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

22. ስለዱር እንስሳት እርባታ

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳትን ማርባት አይችልም፡፡

2. የዱር እንስሳትን በማራባት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ እንዲሁም ከውጭ ሀገር በማስመጣትና በማርባት ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ ለማድረግ ፈቃድ ይሰጣል፡

DRAFT

3. ባለሥልጣኑ ሕልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ እና ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዝርያዎች እርባታ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

4. የዱር እንስሳት እርባታ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሠረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

23. ***በዱር ሕይወትእ ና ውጤቶቻቸው ስለመነገድ***

1. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ከሚሰጠው ፈቃድ ውጪ፤
   ሀ. በዱር ሕይወትና በዱር ህይወት ውጤት መነገድ፣
   ለ. የተዘጋጀ ወይም ያልተዘጋጀ ማንኛውንም የዱር ሕይወት ውጤት መያዝ፣ መግዛት፣ መሸጥ፣ ማስተላለፍ፣ ወደ ሌላ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ የተከለከለ ነው፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከክልሎች ጋር በመተባበር የዱር እንስሳቱ ስርጭትና ብዛት እንዲሁም የንግዱን ተጽዕኖ በመገምገም የሀብቱ ዘለቄታዊነት ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ ያረጋግጣል፡፡

3. በዘቦታ የዱር ሕይወትን በመጠበቅና በማልማት ለሚከናወን የዱር ሕይወት ንግድ በጥናት ላይ የተመሠረተ ኮታን ይሰጣል፡፡

24. ***ስለዱር ሕይወት ጥናትና ምርምር***

1. ማንኛውም የዱር ሕይወትጥናትና ምርምር የሚያከናውን ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

2. የዱር ሕይወት ጥናትና ምርምር ፈቃድ የሚሰጠው ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፤ ሆኖም የጥናት ምርምር ሥራው ከመጠናቀቁ በፊት የፍቃድ ጊዜው ካለቀ ባለስልጣኑ አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብለት ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሊያራዝመው ይችላል፡፡

3. የውጭ ተመራማራዎች በዱር ሕይወት ጥናትና ምርምር ሥራ ላይ ሲሰማሩ ኢትዮጵያውያንን የማሳተፍ፣ የማሰልጠንና የመድን ዋስትና የመግባት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

4. ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የዱር ሕይወት ዘረ-መል ወይም ሌላ አካል በዘረ-መል ባንክ ወይም በሌላ ማቆያ ማስቀመጥ እንዲሁም የዱር ሕይወትን በኢ-ዘቦታ እንዲጠበቅ ማድረግ ይችላል፣

25. <u>ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት</u>

1. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ሊቃለል የማይችል  አሉታዊ ተጽእኖና ሊቀለበስ የማይችል ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸውን እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ የሚቀርብ ማንኛውም የልማት ተግባር ዕቅድ ከዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታው ሥርዓት አያያዝ እቅድ ወይም የልማት ፅንሠ ሃሣብ ጋር የተጣጣመና የተቀመጡትን ገደቦች ያከበረ መሆን ይኖርበታል፣
3. ባለስልጣኑ በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ልማቶች ስርአተ ምህዳሩን ዳግመኛ ሊያገግም በማይችልበት ደረጃ የሚያደርሱ እና ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ሆነው ሲያገኛቸው ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

26.<u>ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች</u>

1. በዱር ሕይወትጥበቃ ቦታ ውስጥ የሚደረጉማናቸውም ኢኮኖሚያዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች የዚህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችንና ድንጋጌዎችን በማይቃረን ሁኔታ መካሄድ አለባቸው፡፡

2. ከዱር ሕይወት ሀብት አጠቃቀም የሚገኘውን ገቢ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የሚጋሩበት መንገድና የአካባቢው ሕብረተሰብ ቀጥተኛተጠቃሚ የሚሆንበት ስልት ይህን አዋጅ መሠረት አድርገውበሚወጡደንቦች ይወሰናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

27.*የዱር ሕይወት ቁጥጥር ሠራተኛ ሥልጣን*

የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ የሚከተሉትሥልጣኖችይኖሩታል፣

1. የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት ይዞ የተገኘን ማንኛውንም ሰው እነዚህኑ ለመያዝ ያስቻለውን ሕጋዊ ፈቃድ እንዲያሳይ የመጠየቅ፤
2. ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤቶች ተደብቀዋል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ወደ ማንኛውም ሰው የመሬት ይዞታ፣ ሕንፃ፣ ድንኳን፣ ተሽከርካሪ፣ የአየር መንኩራኩር ወይም ጀልባ ውስጥ የመግባትና የመፈተሽ እንዲሁም ሻንጣ ወይም እሽግ የመበርበር፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የሚወረሱትን ሀብቶች በቁጥጥር ሥር የማድረግና ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ባወጣው የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት ተገቢውን ደረሰኝ ሰጥቶ የመረከብ፤
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ሲፈጽም ያገኘውን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዞ ለሚመለከተው ሕግ አስከባሪ አካል ማቅረብ

28.*ቅጣት*

1. ማንኛውም ሰው፤

   ሀ. ሕገወጥ የዱር ሕይወት አደን፣ ዝውውር ወይም ንግድ ድርጊት ከፈጸመ፤

   ለ. በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችና መኖሪያ አካባቢያቸው ውስጥ ያልተፈቀዱ ተግባሮችን ካከናወነ ወይም በማናቸውም አኳኋን በነዚሁ ላይ ጉዳት ካደረሰ ወይም ጉዳት ለማድረስ ከሞከረ፣ ወይም

DRAFT

ሐ. የዱር ሕይወትን ወይም የዱር ሕይወት ውጤቶችን ያለፈቃድ ሸሽጎ፣ ይዞና አከማችቶ ከተገኘ፤

ከብር 10 ሺህ በማያንስና ከብር 100 ሺህ በማይበልጥ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

2.ማንኛውም ሰው በሳይተስ ስምምነትበእዝል እንድመሠረት የህግ ከለላ የተሰጣቸው እና ሀገሪቱ በብቸኝነት የምትታወቅባቸውን ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዝርያላይ በማናቸውም ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ከ ሀ እስከ ሐ የተጠቀሱትን የተላለፈ፡-

ከብር 200 ሺህ በማያንስና ከብር 300 ሺህ በማይበልጥ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር አስር ሺህ በማይበልበጥ መቀጮ እና ከሦስት ወር በማያንስ ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ከቅጣቱ በተጨማሪ ከጥፋቱ የተገኘው የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት መሣሪያ ውርስ ሆኖ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፤

## 29. በህገወጥ መንገድ ስለተገኙ የዱር ህይወት ውጤቶች

ሀ. ባለሥልጣኑ የተወረሰውን የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት እንደአግባቡ መሸጥ፣ ለሣይንስ ተግባር ማዋል፣ ለትምህርት ተቋም ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፤

ለ. የተወረሰውን መሣሪያ እንደአግባቡ ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ማስተላለፍ፣ እንዲወገድ ማድረግ ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል ይችላል፤

DRAFT

30.*ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንያወጣል፤

2. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1)መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤

31. *የተሻሩና ጸንተው ስለሚቆዩ ህጎች*

አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና አዋጅ ቁጥር 575/2000 በዚህ አዋጅ ተሸረው ሙሉ በሙሉ በዚህ አዋጅተ ተክተዋል፤

32. **ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

33.*የመብትና ግዴታ መተላለፍ*

የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተቋቋመው ባለሥልጣኑ ተላልፏል፤

34.*አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ*

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ .......ቀን 2008 ዓ.ም.

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

DRAFT